# በከፍተኛ መስዋእትነት የተወለደው ከፍተኛ ኪሳራ!

ከግርማይ ገዛኸኝ

የኢትዮጵያ ህዝቦች ማህብራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፤ ፖለቲካዊ ዕድገታቸውን እንዳያስመዘግቡ የተለያዩ ሥርአቶች ጋሬጣ ሆኖውባቸው እንዲቆዩና እንዳሉ የሚያጠያይቅ አይደለም ። በዚህ ልክ ደግሞ በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜዎች ህዝቦች መብታቸውን ለማስከበር ባካሄዱት ትግል ወደር የለሽ መስዋእትነት ከፍለዋል ። ይሁን እንጂ እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝቦች በመስዋእትነታቸው ያስመዘገቡት ኪሣራ እንጂ የተዋደቁለት የመብት መከበር ሆኖ አልተገኘም ። የትግሎቹ ዓላማዎች የመብት መከበርን ለማዋለድ እንጂ የባሰ የመብት ረገጣን ለማስተናገድ አይደለም ፥ አልነበረምም ። ለዚህ ነው ለዚህ ጽሑፍ በከፍተኛ መስዋእትነት የተወለደ ከፍተኛ ኪሣራ የሚል ርእስ የተሰጠው ።

አሁን ከምንገኝበት መድረክ አንጻር አጠቃላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት አጠቃላይ ሂደቱን መቃኘት አስፈላጊነቱ ባይዘነጋም ፥ የጽሑፉ ይዘት የህወሓት ማዕከለዊ ኮሚቴ ለሁለት መከፈልን የሚመለከት በመሆኑ ህወሓት እንደ ድርጅትና የትግራይ ህዝብ የትግል ድርሻን ከተገኘው ውጤት ጋር በማነጻጸር ላይ ያተኩረ ይሆናል ።

የትግራይ ህዝብ እንደማነኛው የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ብሔራዊ ጭቆና ደርሶበታል ። ብሔራዊ ጭቆናን ከራሱ ለማውረድም ከፍተኛ ተጋድሎ አካሂደዋል ። የዕድል ጉዳይ ሆኖ ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው የውጭ ወረራ በአብዛኛው በሰሜኑ የአገራችን ክፍል እንደሆነ የሚታበል አይደለም ። በዚህ ምክንያትም ትግራ ይበተደጋጋሚ የጦርነት ዓውድማ መሆኑና በዚህም የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈሉን ማብራሪያ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይሆንም ። ይህ ማለት ሌላኛው የኢትዮጵያ ህዝብ አብሮት መዋደቁና የጦርነት ሰለባ መሆኑን በመዘንጋት አለመሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ። ጦርነት በሚካሄድበት አከባቢ የጦርነት ሰለባ የሚሆነው ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቆ የሚጥለውና የሚወድቀው የአገር ጀግና ብቻ ሳይሆን በጦርነት ቀጠናው የሚኖረው ህፃን፥ ሽማግሌ ፥ ወንድ ፥ ሴት ባጠቃላይ የአከባቢውን ነዋሪ እንደሚያጠቃልል ግልጽ ነው ። ከዚህም አልፎ የቤትና የዱር አራዊትንና የአከባቢውን ተፈጥሮን ጨምሮ እንደሚጎዳ የሚያጠራጥር አይደለም ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ በከፈለው መስዋዕትነት ሥልጣናቸውን ያጠናከሩ የገዢ መደቦች ለህዝቦች ያቀረቡት ሥጦታ ቢኖር ህብረተሰብን የባሰ ሰቆቃ ውስጥ መክተት ብቻ እንደነበረ የሚታበል አይደለም ። የትግራይ ህዝብሥጦታም ከዚህ የተለየ አልነበረም ። በዚህም የከፍተኛ መስዋዕትነት ውጤት ከፍተኛ ኪሳራ ማስከተል ነበር ብሎመደምደም ይቻላል ።

## የትግራይ ህዝብ የ17 ዓመት ተጋድሎ ።

የኢትዮጵያ ህዝብ በኢትዮጵያ ገዢ መደቦች የተጣለበትን ኢፍትሃዊነት በማስወገድ ሁሉንም ዜጎቹዋ በእኩል የሚኖሩባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማብሰር ትግል መጀመሩ አማራጭ የሌለው አማራጭ ነበር ። የትግራይ ህዝብ ትግልም የዚህ ትግል አካል ሆኖ ነበር የተጀመረው ። የአፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ በወታደራዊ ኃይል ተተክቶ ያኔም የህዝቦች ጥያቄ ባለመመለሱ የሕብረ ብሔርና የብሔር ድርጅቶች የትጥቅ ትግል በጀመሩበት ወቅት የትግራይ ህዝብ ልጆች እንደየአመለካከታቸው ከብሔራዊ እስከ ሕብረ ብሔራዊ በተደራጁት የፖለቲካ ኃይሎች ውስጥ በመሳተፍ የትግል ግዴታቸውን የተወጡ ከመሆናቸውም በላይ የትግራይ ህብረተ ሰብም በዚሁ ልክ የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ነበረው ። ይህ የትግራይ ህዝብ ትግል ዛሬ እንደነ ጥላሁን ይልማና አሰፋ ነጋሽ የመሳሰሉት ግለሰቦች ሊነግሩን እንደሚቃጡት ጠባብ ብሔርተኝነት የተጠናወተው እንዳልነበረ በግልጽ ያሳየናል ።

የትግራይ ህዝብ ትግሉን የጀመረው ከደረሰበት ብሔራዊ ጭቆናና ካስከተለበት ማህበራዊ ቀውስ ለመውጣት ነበር።በሃገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን ማህበራዊ ቀውስ በመረዳት በወቅቱ የተነሱት ፖለቲካዊ ኃይሎች በጊዜ ደርሰው መልክ ባያስይዙት ኖሮ በንጉሡ አገዛዝ መገባደጃ አከባቢ የትግራይ ወጣት በተናጠል ጫካ እየገባ በሽፍትነት ይሰማራ የነበረበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንደንበረ የሚዘነጋ አይደለም ። ይህ ህብረተሰቡ በነበረው ሥርዓት ላይ ተስፋ ቆርጦ እንደነበረና ህዝባዊ ዓመጽ ሊነሳ በማኰብኰብ ላይ እንደነበረም ያመላክታል ። የትግራይ ህዝብ ስሜት ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ላይ እያለነው እንግዲህ የህወሓትም ሆነ የሌሎች ፖለቲካዊ ኃይሎች ብረታዊ ትግል የተጀመረው ። ለዚህም ነበር የትግራይ ህዝብ የተጀመሩትን ትጥቃዊ ትግሎች እልል ብሎ ተቀብሎ ያስተናገደው ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በትግራይ ውስጥ በትግል ሜዳ ላይ ስለተሳተፉት ድርጅቶች ዝርዝር ጉዞ ማቅረብ ባለመሆኑ በህወሓት ድርጅታዊ አመራር ሥር የተጠናቀቁትን 17 የትግራይ ህዝብ የተጋድሎ ዓመታት ላይ በማትኩር ይቀጥላል ።

የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ እኩልነቱ ለማረጋገጥ ትግል መጀመሩ ተወስቷል ። ለዚህ ትግል የታለመለት ግብ መምታት የትግራይ ህዝብ አስተዋጽኦ በንዋይ አቅርቦትና በስነ ልቦናዊ ድጋፍ ላይ ብቻ የተመሠረተ አልነበረም። የትግራይ ህዝብ ከህወሓት ጋር በአካል በመሰልፍ ውድ ህይወቱን ከፍለዋል ። ደሙን አፍስሰዋል አጥንቱን ከስክሷል ። የሚያፈቅራቸው የውድ ልጆቹን ህይወት በመቶዎች ሳይሆን በሺዎች ገብሮበታል ። ቤት ንብረቱ ጋይቷል ። ሰላማዊ ኑሮው ጠፍቶ ከአይሮፕላን ቦምብና ከከባድ መሣሪያዎች ድብደባ ለማምለጥ ዋሻና የቀበሮ ጉድጓዶችን መኖርያ ቤቱ አድርጓል ። የሰው ልጅ ቀን እየሠራ ሌሊት የማረፍ የተፈጥሮ ባህሪ በሆነበት ዓለማችን የትግራይ ህዝብ ከቀን ጥቃት ራሱን ለማዳን ሌሊት እየሠራ ቀን በዋሻና በቀበሮ ጉድጓድ እየተደበቀ ኑሮውን የገፋበት ሁኔታ እንደነበረ እንደፋቅ ታሪክ ተደርጎ የሚተረክ ሳይሆን ይህ ትውልድ የራሱን ምስክርነት ሊሰጥበት የሚችል ሃቅ ነው ። የትግራይ ህዝብ ይህንን ስቃይ የተቀበለው የአቶ መለስና የአቶ ስብሓት የግል አጀንዳ የነበረውን መገንጠል የሚለውን አባዜ ለማተግበር አልነበረም ። በተቃራኒው የሁለቱ ግለሰቦችን የመገንጠል በማያዳግም ሁኔታ ለማንሠራራት በማይችልበት መንገድ መትቶ በትግሉ ያመከነው

የትግራይ ህዝብ እንጂ ሌላ ማንም አይደለም አልነበረምም ። የትግራይ ህዝብ የትግል ታሪክ ዛሬ በአሰፋ ነጋሽ መጽሓፍና በአሰፋ ነጋሽ መጽሓፍ አድናቂዎች የሚነገረው ዓይነት ቢሆን ኖሮ የነአቶ መለስ እኩይ አጀንዳ በተግባር ከመዋልየሚያግደው ነገር እንዳልነበረ የሚያከራክር አደለም ። የትግራይ ህዝብና ጀግና ታጋይ ልጆቹ ክቡር መስዋእትነቱን የከፈሉት ሰው ከሰው ብሔር ከብሔር ብሐረሰብ ከብሔረሰብ የማይበላለጡበት ፣ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ፣ፖለቲካዊና ሰብአዊ መብቶች የተከበሩባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመገንባት ነበር ። የትግራይ ህዝብ የትግል ዓላማ ይህ ባይሆን ኖሮ የመገንጠል ዓላማ ኣቀንቃኞች ዛሬ ዓላማቸውን በተግባር ኣውለውት ነበር ። የትግራይ ህዝብ ልጆችም ጓዴ ካንተ በፊት ያርገኝ እያሉ ከደርግ ሥርዓት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቀው ውድ ህይወታቸውን ለመስጠት ባልተዘጋጁና ባልሰጡ ነበር ። በህወሓት መሪዎች የብልጣብልጥነት አመራር ሺዎች የተሰዉለት ዓላማ ግቡን አልመታም ማለት የተሰዉትን የሚያስወቅስ ሳይሆን ፣ እኛን የቀረነውን ትዝብት ውስጥ የሚከት ነው ። እነሱግዳጃቸውን ተወጥተው አልፈዋል ። በህዝባዊ ዓላማ ላይ ቆመው ለህዝባዊ ዓላማ ራሳቸውን አስገዝተው አልፈዋል ። የተሰውለት ዓላማ ህዝባዊ ዓላማ እንደነበረ ለምንቀበለው ወገኖች አደራውን ተረክበን የታለመለትግብ ማድረስ በኛ በህይወት ባለነው ላይ የተጣለ ግዳጅ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ። ከዚህ ሂደት የትግራይህዝብ ህወሓትን እንዴት አቅፎ ደግፎ ህይወት ገብሮ ለተሸራረፈ ድል እንዳበቃው ለመገንዘብ ይቻላል ። የህወሓት አመራር በትግራይ ህዝብ ልጆች ደም የወታደራዊ ደርግን ሥርዓት በመገርሰስ ለሥልጣን በቃ ።

እዚህ ላይ የትግራይ ህዝብ የትግል ድርሻን በማንሳት የህወሓት/ማሌሊት አመራር ተግባራት ሳያጋልጡ ማለፍ ሀተታውን ያልተሟላ ያደርገዋል ።

የህወሓት አመራር ዴሞክራሲያዊ አወቃቀር ያልነበረው ከመሆኑም በላይ የትግል ግዴታቸውን ለመወጣት ወኔውም ቆራጥነቱም ያልነበራቸው ወይም የሌላቸው ከጆሮ ጆሮ በማንሸኳሸክ ቆራጡን ታጋይ ኃይል በመከፋፈል የሚያሽመደምዱ ፣ በመርህ ላይ የተመረኮዘ የጠራ ዓላማና ራእይ የሌላቸውና ያልነበራአቸው ወገኖችን አቅፎ ይጓዝ የነበረና እየተጓዘም ያለ ኃይል ነው። አመራሩ ውስጥ ህዝባዊ ዓላማ አንግበው የሚጓዙ የነበሩና አሁንም ያሉ ቢሆንም እነዛ መልቲዎች በዓላማ ኣንጋቢ ሀቀኛ ታጋዮች ላይ ያነጣጠሩት መርዘኛ ጦር መኖሩን በጊዜ ለመገንዘብ አልቻሉም ። የዓላማ ቢሶች ዓላማ ለሥልጣን መቋመጥ ነውና ቆራጡ ወገን ለዓላማው ሲዋደቅ እነሱ ትግሉን ትተው የሥልጣናችው መንገድን ሲያመቻቹ ነብር። ለዚህ ግብም ያለ የሌለ የተኮል ሴራ ሲያውጠነጥኑ ነበር ። እነዚህ ሰዎች በሂደት ሥር እየሰደዱ ታጋይ ኃይልን በማሽመድመድ የድርጅቱን ከፍተኛ ሥልጣን እስከመያዝ ደረሱ ። በመጨረሻም የድርጅቱን መዋቅር ጠቅልለው በቁጥጥራቸው ሥር አስገቡ ። ለእኩይ ተግባራቸው መሣሪያ የሚውል ለምን የሚል ጥያቄ የማያነሳ አድርባይ ኃይል በስፋት ተመለመለ ። ይህ ኃይል ሃቀኛታጋዩን ለመምታት ተጠቀሙበት ። የሰፊው ህዝብ የትግል ዓላማና ግብ ለነሱ ጥቅም እንዲውል ተመቻቸ ። እነዛ የተመለመሉት አድርባዮች ህሊናቸውን ለግለሰቦች ሸጡ ። የህወሓት መሪዎች ልሳንና ተግባሩ ተለያዩ ። የህወሓት አመራር በልሳኑ የሰፊው ህዝብ አጋር ሆኖ ለመታየት ዘላበደ ፣ ጻፈ ሰፊው ህዝብን አታለለ ። ተግባርና ልሳን ለየቅል የሆኑበት ህዝብና ታጋይ ጥያቄ ማንሳት ጀመሩ። ለአድርባይ ካድሬ ሥራ ተፈጠረ ። ስለላና አፈና በሀቀኛ ታጋዩና በህዝብ ላይ አነጣጠረ ። ህዝብና ታጋይ በፍርሓት ተዋጡ ። ሰፊው ህዝብና ታጋይ ልጆቹ የውሳኔ ባለቤት መሆናቸው ቀርቶ የአመራሩን ፍላጎት ለመፈጸም የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጠረ ።ህዝባዊ ትግል ለጥቅም ባኰበኰበው የህወሓት/ማሌሊት አመራር ተጠለፈ ። የትግሉ ሂደት ላይ ጥያቄ ያነሳ ታጋይና ህዝብ ሁሉ ለወርዒና ለፃኢ ጉድጓዶች እስርቤት ተዳረገ ። የስንቱ ታጋይ ህይወት በከንቱ አለፈ ፣ ባከነ ። ስንቱ ህዝባዊ ራእዩ እንደ ሓጥአት ተቆጥሮበት ስም በማጥፋት ተዘመተበት ። የህወሓት/ማሌሊት መሪዎች የህዝቡና የሰፊውን ታጋይ መስዋእትነት ለራሳቸው በመዝረፍ በማሌሊት አመራር የተበሰረ ድል እያሉ በየመድረኩ ማላዘንን እንደዋና ሥራ ተያያዙት። የሰፊው ህዝብ ትግል ተጨናገፈ። የህወሓት/ማሌሊት ገመናን ዘርዝሮ ለማስቀመጥ አይቻልም ። በመጠኑ ለመጥቀስ የተሞከሩት ጭብጦች የእያንዳንዱን አንባቢ ህሊና የበለጠ ለመመራመር እንደሚያነሳሱት ግን አያጠራጥርም ። ይህ ማለት ግን ይህንን ፀሓይ የሞቀውን ሀቅ ሚክድ የለም የሚል የዋህ አመለካከት አለመኖሩ ሊሰመርበት ይገባል ። እዚህ ላይ ዋናው ዓላማ የህወሓት/ማሌሊት አመራር ህዝባዊ ትግሉን ለራሱ ጥቅም እንዴት እንዳዋለው ለማሳየት መሆኑ ግንዛቤ ማግኘት ይኖርበታል ።

እንግዲህ የትግራይ ህዝብና የታጋይ ልጆቹ መስዋዕትነት ከጅርጅቱ መሪዎች በአንጻራዊነት ሲታይ ምን እንደሚመስል ባጭሩ ከላይ ተገልጿል ። የትግሉ ውጤት ከደርግ መፍረስ ማግስት ጀምሮ ምን እንደሚመስል መቃኘቱ የትግሉ ውጤት አጠቃላይ ሥዕል ለማየት ይረዳል ።

## ኢህአዴግ በመንግሥትነት ።

የኢህአዴግ ወሳኝ አጋር ወይም ሞግዚት የሆነው የህወሓት/ማሌሊት አመራር የትግል ሂደት ምን ይመስል እንደነበረ ከዚህ በላይ ለማየት ተሞክሯል ። ዛሬ ያለ የህወሓት መሪዎች አመራር ኢህአዴግ የሚባል ነገር እንደሌለ ግልጽ ያልሆነለት ወገን ካለ ለመቀበል ፍላጎት የሌለው ብቻ መሆን አለበት ። ሌሎች ድርጅት ተብየ የኢህአዴግ አባሎች ተሊኮ ከማስፈጸም ያለፈ ድርጅታዊ ህልውና እንደሌላቸው ግልጽ ሆኗል ። የህወሓት/ማሌሊት መሪዎችም ተክነውት የመጡትን ኢኛ ዴሞክራሲያዊ ባሕሪያቸው ባገር ደረጃ ለማተግበር ዕድሉ ገጥሞዋቸዋል ፣ እየሠሩበትም ናቸው ።

በዚህ መሠረትም ዛሬም እንደ ትላንቱ ለውጭ ታዛቢ ማታለያ የሚሆነውን ተውኔት ለማዘጋጀት አልተቸገሩም ። የደር ሥርዓትን በማፍረስ አዲስ አበባ እንደገቡ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም በሚል ለማስመሰያ አገልግሎት ኮንፈረንስ ተብየ ተውኔት አዘጋጁ ። የኮንፈረንሱ ዓላማ ለአገር የሚበጅ አጀንዳ ይዞ ለመውጣት ሳይሆን የአሜሪካ መንግሥት ይሁንታን ለማግኘት የተዘጋጀ ተውኔት ስለነበረ በዓላማ አነሳሽነት የተመሠረቱ ፣ ለዓላማ መስዋእትነት የከፈሉ የፖለቲካ ኃይሎች እንዳይሳተፉ ታገደ ። የህወሓት/ማሌሊት መሪዎች ቅድሚያ የሚሰጡት ለግል ጥቅማቸው ነውና ለዛ ኮንፈረንስ ተብየው ነገር ተሳትፎም ድርጅቶችን ማቋቋምና ማፈላለግ ጀመሩ ።

በዚህ መሠረትም የህወሓት መሪዎች ለዓላማቸው ግብ ይረዳሉ የሚሉዋቸውን የፖለቲካ ድርጅቶችን መፈልፈልና ማስፈልፈልን ተያያዙት ። ላቀዱት ግብ የሚያገለግሉ ድርጅቶችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፈጠሩ ። ኮንፈረንስ ተካሄደ ። በድል ስለመጠናቀቁም በስፋት ተስተጋባ ። ህዝባዊ ውክልና የሌላቸው ኃይሎች ተሰባስበው የኤርትራ መገንጠልን እውን አደረጉ ። የሽግግር መንግሥት ተብሎ የሽግግር ጊዜ ቻርተር አጸደቀ። ጉዞው በዛው ቀጠለ ። ውሾች ይጮኻሉ ግመሉ ግን ጉዞውን እየቀጠለ ነው የሚል ዘፈን ተዘመረ ። እውነትም ግመሉ ጉዞውን ቀጠለ ። አቅጣጫው ያልታወቀ ጉዞ በርምጃ ሳይሆን በዝላይ ተጀመረ ። የሽግግር መንግስት ጉዞውን ወደ ገደል ጀመረ በማለት ያገሩ ጉዳይያሳሰበው ህዝብ ገና በጊዜ ማስጠንቀቅ ጀመረ ። ሰሚ ጠፋ ። የሽግግር ጊዜው ገና ሳይገባደድ እነ ኦነግ አደናቃፊ ፤ ጠባብ ተብሎ ከሜዳ ለመውጣት ተገደደ ። በሸፍጥ ምርጫ የሕገ መንግሥት ለማጽደቅ ህዝብ ተወካዮቹን መረጠ ተብሎ ተነገረ ። ሕገ መንግሥት ተብሎ ሰነድ በወረቀት ሰፈሮ ጸደቀም ተባለ ። በተግባር ግን ቻርተሩም ሆነ ሕገ መንግሥቱ ፍሬአቸው ሳይታይ ቀረ ። ራሱ ያጸደቃቸውን ሕጎች በመጣስ የኢህአዴግ አመራር የመጀመሪያ ሆኖ ተገኘ ። የዜጎች መብት ተገፈፈ ። የሕግ ያለህ የሚል ጩኸት በረከተ ። ያለፍርድ መታሰር ፤ ታፍኖ መድረሻው ሳይታወቅ መቅረት ፤ ዜጎች ላይ ያልዋሉበት ወንጀል ለጥፎ ማሰቃየት ፤ ህይወቱን ሰጥቶ ለሥልጣን ያበቃውን ታጋይ ማሸመድመድ ፤ ማሰር ፤ ማባረር ፤ ስም ማጥፋት ፤ መግደል ፤ — ወዘተ የዕለት ተዕለት የኢህአዴግ መሪዎች ተግባር ሆነ ። የአገሪቱ ኢኮኖሚ በኢህአዴግ ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር ገባ ። ሕግ ጠፍቶ የኢህአዴግ መሪዎች ፍላጎት ሕግን ተካ ። ሃገር በዘር ተሸነሸነች ። ሙስና ፤ በዘመድ መጠቀም ፤ የኢህአዴግ ሥርዓት ዋና መለያ ለመሆን በቃ ። የኢህአዴግ ካድሬዎች እንደመሪዎቻቸው እንዳቅሚቲራሳቸውን ከሕግ በላይ አድርገው ተመለከቱ ። መንግሥት ሆኑ ። በተለይ የትግራይን ሁኔታ ቀረብ ብሎ ለተመለከተ የካደሬ ሥልጣን የደረሰበትን ደረጃ ለማየት ችግር አይሆንም ። ትግራይ ውስጥ ካድሬ የሁሉም ነገር የሰው ህይወትም ጭምር ወሳኝ ነው ። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲመዘን ካድሬ አምራች ኃይል አይደለም ። የባሰው ራሱ አምራች አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን አምራቹን ህዝብ ስብሰባ ኢያለ ሥራ ማስፈታቱ ነው ። ለዛም የአብዛኛው የእውቀት ምንጭ የአቶ መለስ ዜናዊ ጽሑፍና ወይን ጋዜጣ ብቻ መሆኑ ሳይዘነጋ ነው ። ባጭሩ የግለሰቦች ተልእኮ አስፈጻሚ እንጂ የሥርዓት ገንቢ አካል ሊሆን የሚችል ኃይልአይደለም ። ሐሳብን በነጻ የመግለጽ መብት በአቶ መለስ ካድሬዎች ፍላጎት የሚፈቀድና የሚከለከል ችሮታ ሆኖ ተቆጠረ ። ሓሳብን በነጻ መግለጽ በተግባር ሲታይ የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጦች ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለውን በደል መመልከቱ ይበቃል ። የኢትዮጵያ ህዝቦች አበሳ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም ። የቀረውን አንባቢ ራሱ ያክልበት ። የከፍተኛ የመስዋእትነት ውጤት ምን ያህል የከፋ አበሳ እንዳስከተለብን ለማየት ግን ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ብቁ የሆናል ።

## የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ለሁለት መከፈል ።

የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ለሁለት መከፈል እውን ከሆነ ሰንበትበት ብለዋል ። ለሁለት የመከፈሉ አባዜ ግን የተለያየ ትርጉም ይዟል ። የነ አቶ መለስ ዜናዊ ቡድን ከነካድሬዎቹ ከማእከላዊ ኮሚቴው ቁጥር አንፃር ሲታይብዙሓን የነ አቶ ተወልደ ወልደማርያም ቡድን ውሁዳን ተብሎ ተመድበዋል ። ከህዝብ ድጋፍ አንፃር ሲታይ ግንየብዙሓንና ውሑዳን አመዳደብ እነ አቶ መለስ ከሚነግሩን የተለየ ሆኖ ይታያል ። እነ አቶ መለስ 20 ወይም 30 ሰው ታገደ እንጂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እክል አላጋጠመውም ይላሉ ። በተቃራኒው የነአቶ ተወልደ ቡድንናደጋፊዎቹ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመውደቅ አደጋ ገጥሞት እየተንገዳገደ ነው ይላሉ ። የመውደቅ አደጋ ደርሶበትበመንገዳገድ ላይ የሚገኘው ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ላይ ልዩነት ቢኖርም የመፍረስ አደጋ ገጥሞታል የሚለው ላይ እውነት እንዳላቸው አያጠያይቅም ። እየፈረሰ ያለው ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው የሚለው አባባል ግን ከላይ የተቀመጡትን አዴሞክራሲያዊ ተግባራት የሚያራምድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊኖር ስለማይችል አስተሳሰቡ በጽንሰ ሓሳብ ደረጃም አደገኛ ነው ።

በመሠረቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ህዝባዊ ባህሪን ይዞ ስለሚጓዝ በህዝብ ፍላጎት የሚመራ ሥርዓት በመሆኑ እንዲሁ ግለሰቦች ከድርጅት ስለለቀቁ ወይም ባሁኑ ሁኔታ ሲታይ ስለተወገዱ የሚፈርስ አይደለም ። እንኳን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊም ሳይሆን ላወጣው ሕገ መንግሥት ተገዢ የሆነ ሥርዓት አይፈርስም ። ስለዚህ ዛሬ በኢትዮጵያ በመፍረክረክ ላይ ያለው ሥርዓት ዴሞክርራሲያዊ ሥርዓት አይደለም ፤ አልነበረምም ። በመፍረክረክ ላይ ያለው ሥርዓት አምባገነናዊ ሥርዓት ነው ። አምባገነናዊ ሥርዓት ላጸደቀው ሕግ መገዛትን አያውቅም ። ራሱን ከሕግ በላይ ያስቀምጣል ። የህወሓት አመራርም ራሱን ከህግ በላይ አስቀምጧል ፤ ዛሬም በዛው ሲቀጥል እንጂ ለሕግ ተገጅ ሲሆን አይታይም ። የህወሓት አመራር ጥፋት በዘር እንደሚተላለፍ በሽታ አድርጎ ይቆጥረዋል ። አንድ ሰው በህወሓት አመራር በሆነ ምክንያት ከተጠላ ዘመድ አዝማዱ በሙሉ ጠላት ተብሎ ይፈረጃል ። በዛም በጅምላ ማዋከቡ ይቀጥላል ። የህግ ያለህ አይሠራም ። በነተክሉ ሃዋዝ ፤ በነሐጎስ አጽባሃ ፤ በዓጋመ አውራጃ ውስጥ በአቶ ተስፋይ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ የደረሰውን ይጠቅሰዋል ። በአሁኑ ሰዓት ተወገዱ በተባሉት የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ቤተሰብና ዘመድ አዝማድና ወዳጆች ላይ እየደረሰ ያለውን ልብ ብሎ መገንዘቡ ቋሚ ምስክር ይሆናል። ይህ የህወሓት አመራር ተግባር ህግና ሥርዓትን ይጻረራል ብቻ ሳይሆን ራሱ ይመቸኛል ብሎ ያወጣው ህግንም ይቃረናል ። ታዲያ ይህ ራስን ከህግ በላይ ማስቀመጥ ካልተባለ ምን ሊባል ይችላል ? ይህን ሥርዓት አምባገነን ሥርዓት ከመሆን ውጭ ምን ሥርዓት ሊሆን ይችላል ? ይህ ሥርዓት በማያሻማ አምባገነን ሥርዓት ነው። አምባገነናዊ ሥርዓት ላይ ቆመን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ደግሞ የማይታለም ፤ የማይጠረጠርም ነው ። ሥርዓቱ አምባገነናዊ ሥርዓት በመሆኑ አሁን የታየው ክስተት ባጋጣሚ የመጣ ሳይሆን የሥርዓቱ ውጤት መሆኑ መታመን አለበት ። ስለዚህም ትግሉ ለሥርዓት ለውጥ መሆን ኣለበት ። እዚህ ላይ ሌላ የሚነሳ ነጥብ ኣለ ። ይኸውም ህግ ተጥሰዋል ወይ የሚል ነጥብ ነው ። አዎ በማያሻማ መንገድ ሕግ ተጥሰዋል ። ሕግ ያልተጣሰው መቼ ነው የሚለው ጥያቄ ግን አብሮ መነሳት ይኖርበታል ። የድርጅቱ ህገ ደንብ ያልተጣሰበት፤ የድርጅቱ አባላት በድርጅቱ ህግ ላይ የተመረኮሰ ብይን ያገኙበት ፤ የድርጅቱ አባላትም ሆኑ ሰፊው ህዝብ

እኩል የፍትህ ተጠቃሚ የሆኑበት ጊዜ አልታየም። ከድርጅቱ አመራር ጀምሮ እስከ ተራ ታጋይና ሰፊው ህዝብ ድረስ በህገ ወጥ መንገድ ቁጥር ስፍር የሌለው ሰቆቃና ግፍ የደረሰባቸው የድርጅቱ የተጻፈ ህግ ስለ ሚፈቅደው አልነበረም ። ለሥልጣን ካደረሱ በኋላ በፈጠራ ውንጀላ ከድርጅቱ ስለተባረሩ ታጋይ ወጣቶች፣ በየእስር ቤቱ እየማቀቁ ስለሚገኙ ንጹሓን ዜጎች ድምጽ አልተሰማም ።ዛሬ የተጣሰው ህግ ግን ያኔም ተጥሰዋል ። ስለዚህ ህግ የተጣሰው ዛሬ ለመጀመሪያ አለመሆኑና ያኔ ባለመጮኻችን ለዛሬው ችግር መዳረጋችን ከፍተኛ ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል ። በበኩሌ ከዚህ በፊት እነዛ ጥፋቶች ሲደርሱ እንደዛሬ ድምጼን ከፍ አርጌ ለነዛ ወገኖቼም ባለመጮኼ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ ሁልም የግፉ ሰለባ የሆኑ ወገኖቼን እጠይቃለሁ ። እንግዲህ ዛሬም እንደወትሮው የድርጅቱ ህግ ተጥሷል ። የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ቡድን ሥልጣኑን ከአገባብ ውጭ ተጠቅሞበታል ። ሁለት በይቅርታ አቶ መለስ ጉያ ውስጥ የተመለሱትን ጨምሮ 12 የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት በ16 የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ታግደል ። ከ12 ውስጥ 5ቱ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ናቸው ። ይህ ሲመነዘር 4 የሥራ አስፈጻሚ አባላት 5ቱን የሥራ አስፈጻሚ አባላት አገዱ ማለት ነው ። እግዱ በዚህ አላበቃም ። እላይ እንደተጠቀሰው የህወሓት አመራር ሓሳብና ግለሰብን ለይቶ ለማየት ስለማይችል ፣ ዛሬ የታገዱት ወገኖች ጋር ግንኙነት የነበረው ሁሉ የነሱን ጽዋ በመጎንጨት ላይ ይገኛል ። የአቶ ገብሩ አሥራትና የአቶ ዓለም ሰገድ ገብረአምላክ ባለቤቶች የባለቤቶቻቸው አመለካከት ሰለባ ሆነዋል ። እግዱ ለህወሓት ኦዲት ኮሚሽንም ተርፏል ።
በዚህ ማኸል ስማቸው የማይጠቀስ ስንት ንጹሃን ሰለባ ሆኗል እየሆኑም ነው ። የአቶ መለስ ካድሬዎችም ለትግራይ ህዝብ ተናካሽ ውሻ ሆነውበታል ። የትግራይ ህዝብ የታገዱት አባላት የሚሉትን እንስማ ብለዋል ። የአቶ መለስ ካድሬዎች ደግሞ የትግራይን ህዝብ እኛ ከተናገርነው ውጭ እንዳትሰማ በማለት ቁም ስቅሉን እያሳዩት ናቸው ። ፍጥጫው እስከመቼ እንደሚዘልቅ በውል ለመናገር ባይቻልም ብህዝብና በካድሬ መካከል ፍጥጫው ቀጥለዋል ። የህዝቡ አመለካከት ባሸናፊነት የካድሬው በተሸናፊነት ፍጥጫው እንደሚጠናቀቅ ግን አያጠራጥርም ።

## <u>የተፈጠረው ቀውስና መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ።</u>

በህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ውስጥ የነበረው መግባባት ጠፍቶ ፣ የአቶ መለስ አምባገነንነት ጣራውን እየነካ ባለበት ወቅት ላይ ነን ። የአቶ መለስ አምባገነንነት ከፍ ከፍ እያለ ሲመጣ የተቃውሞ ትኩሳትም በከፍተኛ ደረጃ እየተቀጣጠለ ሲጓዝ እየታየ ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው ከዚህ በፊት ተከስተው ለነበሩት ህገወጥ የህወሓት አመራር ተግባራት በጊዜ ተገቢ ምላሽ ባለመስጠታችን ለዛሬው ህገ ወጥ ተግባር ተዳርገናል ። ትላንት ህገወጥነትን አውግዘን ቢሆን ኖሮ ዛሬ መጮኽ ባላስፈለገን ነበር ። ነገሮች የሚጀምሩት ባንድ ቦታና አጋጣሚ በመሆኑ ህገወጥነትን መታገል ዛሬ መጀመሩ በቀጣይነት ሊከተል የሚችለውን ከፍተኛ አደጋ ለማስወገድ የሚያስችለን ወሳኝ ምዕራፍ ይከፍታል ። ስለዚህም መበርታትና መበረታታት ይኖርበታል ። ትንሽ ትልቅ ፣ ሴት ወንድ ፣ ብሔር ብሔረሰብ ወዘተ ሳይለይ ዜጎችን በእኩልነት የሚዳኝ ሥርዓት መፈጠር አለበት ።«የጎረቤቴ ቤት ሲቃጠለ ካየሁ የኔ ቤት አደጋ ላይመሆኑን እገነዘባለሁ» የሚለውን የአንድ ጀርመናዊ ጠበቃ አነጋገር ልብ ሊባል ይገባል ። ሕግ የበላይነቱን ማረጋገጥ መቻል አለበት ። ሕግ ለንጉሥ ፣ ለፕረዝደንት ፣ ለጥቅላይ ሚኒስትር ፣ — ወዘተ ለመሳሰሉ ባንድ አገር በትረ ሥልጣን ለጨበጡ ቢቻ የሚያገለግል መሳሪያ ሲሆን ሥርዓት ማስፈን ፣ የጋራ ዕድገት ፣ የአገር ግንባታና ተፋቅሮ መኖር የሚባሉ ጉዳዮች ቦታ አይኖራቸውም ። የህብረተ ሰብ ቅራኔዎች በሕግና በፍትሃዊ መንገድ ለማስተናገድ ካልተቻለና ህዝቦች ባገራቸው የጋራ ተጠቃሚ ለመሆን እስካልበቁ ሰላም ይኖራል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይሆናል ። ዞሮ ዞሮ በሕግ የበላይነት እስካልታመነ ድረስ የሚገኘው ሰላም ዕለታዊ እንጂ ዘላቂ ሊሆን አይችልም ። ያለዘላቂ ሰላም ደግሞ ዘላቂ ሥርዓት መገንባት ሊሞከር የማይታሰብ ነው ። ይህ ከሆነ ዘንዳ መታገል ለፍትህ መንገሥ እንዲሆን የግድ ይላል ።
የአንድ ዜጋ ፍትሕ የሚነፈግበት ሥርዓት ሥርዓት ሊሆን አይችልም ። ላንዱ ዜጋ የተነፈገ ፍትሕ ለሌላ ዜጋ እንዲሠራ መጠበቅ ፍጹም የማይቻል ነው ። ከዚህ በመነሳት ባሁኑ ሰዓት አቶ መለስና ተከታዮቻቸው በታገዱት የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና ወዳጅ ቤተሰብ ላይ እያደረሱት ያለው ሕገ ወጥ ተግባር ማስቆም መቻል አለበት ። ይህ መከናወን የሚኖርበት የታገዱት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት ላይ ስለነበሩና ሂደቱ እንዳይተጓጉል ተብሎ ሳይሆን በመርህ ደረጃ የሕግ የበላይነት እንዲከበር የሚካሄደው ትግል አካል በመሆኑ ነው ። እነሱ በሥልጣን በነበሩበት ወቅት ለሕግ የበላይነት መከበር ተገብ ትግል አካሂደው ቢሆኑ ኖሮ ዛሬ እየደረሰባቸው ያለው ሕጋዊ ያልሆነ የመብት ገፈፋ ሊደርስባቸው ይችል ነበር ብሎ ለመገመት አይቻልም ። ዛሬ በነሱ ላይ የደረሰው ኢሕጋዊና ኢፍትሓዊ ተግባርም መታገል የሚኖርብን የነሱን ሕጋዊ መብት ማስከበር ስላለብ ብቻ አይደለም ፣ መሆንም የለበትም ። ዛሬ ለነሱ መብት መታገል ማለት በቀጥታ ለራስ መብት መከበር መታገል ጋር የሚቆራኝ ስለሚሆን ነው ። እያንዳንዱ ለፍትሕ ቁሜአለሁየሚል ዜጋም የፍትሕ መከበርን እንደመርህ በመከተል ሁላችንን የሚያቅፍ ማህበራዊ ፍትሕ እንዲሰፍን ቅድሚያ በመስጠት የተሟላ ህዝባዊ ድል ለማበሰር መታገል ይጠበቅብናል ። እነ አቶ መለስም ቢሆኑ አላወቁበትም እንጂ ሕግ ማክበር የሚጠቅመው ቅድሚያ እነሱን ነበር። የህዝባችን ትግል ዛሬም እንደወትሮውተኮላሽቶ ብልጣብልጦች እጅ እንዳይገባ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ የግድ ይላል ። በመርህ ደረጃ ለፍትሕ መታገል የእያንዳንዱን የህብረተሰብ አባል ሕጋዊ መብት እንደሚያስከብር አያጠራጥርም ና ፍትሕም ሰውን አይለይምና ለፍትህ እንታገል ። የህዝባችን መስዋዕትነት ዛሬ ለዘላቂ ድል መሆን ይኖርበታል ።

ለህዝባዊ ድል የተከፈለው የወገኖቻችን ደም
ለግለሰቦች መከበርያ አይውልም ።
ድል ለሰፊው ህዝብ ።